# «ያማ ሞቶ» አይቀር!

(ወደ ያንኪዎች አምባ ያነጣጠረ ቅኔ ከገሞራው)

እንዴው እንበል እንጂ - ከጉድም ጉድ ነገር፣
ሰው እየጨፈጨፈ - እያጠፋ ሀገር፣
እሱ አለሁ ቢልም - «ያማ ሞቶ» አይቀር!

ማነው ያደረገው - ፈላጭና ቆራጭ?
የወገናችንን - ደመ-ነፍሱን መጣጭ፣
ሲገሠግሥ ገብቶ - ከሀገር ድንበር ውጭ፣
እንዲህ የሚጫወት - ሥጋ አጥንቱን ሲነጭ!

እንዲያ እያሠቃየ - ነፍሱን ፈፋ ሲጥል፣
«ያማ ሞቶ» አይቀር - ደም መላሽ ያገኛል፣
ፍርድ የመጣለታ - ፍዳውን ይከፍላል።

“A valuable strategic relation አለን ከእኛ ጋር፣
እያለ ያንኪው ሰው - እንደዚያ ሲያጓጉር፣
ስንቱን ነፍስ አጠፋ - በከንቱ ግርግር፣
የመጣው ይምጣ እንጂ - በሰማይም በምድር፣
የፈለገው ቢሆን - «ያማ ሞቶ» አይቀር!!

አንድ ቀን ይመጣል - የምድር የሰማይ ፍትሕ፣
«ያማ ሞቶ» አይቀር - ግፍ መዛኙ አላህ!
ዶጋመድ ያደርጋል - ፅዋው የሞላለት -
ሳይል ወዲያ ወዲህ!

አይቀርም ይመጣል - ያንድዬ ቀጭን ፍርድ፣
አርምሞ አያይም - ታላቅ ሕዝብ ሲዋረድ!

የቀኑ ቀን ለታ - ያሳያል ተዓምር፣
«ያማ ሞቶ» አይቀርም - ይፋረዳል በቀል!!

ሲቀልድ አይኖርም - «ያማ ሞቶ» ወገን፣
አንዴ ይደፋዋል - ሲደርስ የራሱም ቀን።

«ለሁሉም ጊዜ አለው!» - የተባለው ብሒል፣
ተረት አይመስለኝም - በኛ በሰዎች ባሕል።

ይመጣል አንድ ቀን - እየገሠገሠ፣
«ያማ ሞቶ» አይቀርም - ደም እንዳፈሠሠ፣
ምንጊዜም ሕያው ነው - ፍርድ የተንተራሰ።

“Go ahead & smash the brains of ardent Nationalists
& Communists…!” እያለ ሲመክር፣
ባልወለደ አንጀቱ - ንፁሐን ሲዘርር፣
«ያማ ሞቶ» አይቀርም - የጠፋው በአሣር፣
አንድ ቀን ይነሣል - ገዳዮች ሊከምር!

በሃቅና በርግጥ - «ያማ ሞቶ» አይቀርም፣
ወገን ሀገር ገድሎ - ሰላም ውሎ አያድርም!
ያገኛል ዋጋውን - በውድም በግድም፣
የዓለም ባሕርይ - ለገዳይ አይሠግድም፣
ላረመኔ ጨካኝ - ፍትሕም አያረግድም፣
ይከሥማል አንድ ቀን - «ያማ ሞቶ» አይቀርም!!

ቻይናዊ  ሲሳደብ - «ሁዋይ-ዳን» ነው ይላል፣
መበስበሱን አውቆ - ሲዘገይ እንቁላል።
ይኸም የሚቆየው - እስከዚያው ድረስ ነው፣
በስብሶ ይፈርሣል - ኬላው ሲደርስ የዕድሜው።

ቀልቡና ውቃቤው - የንፁሕ ሕዝባችን፣
ተንጠልጥሎ አይኖርም - በታላቅ ሠቀቀን፣
ጠዋት ማታ ሲማለል - ርትዕና ፍትሕን፣
እየደረሰ ነው - ዕሴት ማምረቻው ቀን።

እስከዚያው ድረስ ግን - «ያማ ሞቶ» አይቀርም፣
ዋጋውን ያገኛል - በዳይ ሰው ምንጊዜም!!
በምንም ቢመዘን - ገዳይ ገድሎ አይኖርም!

____________ X0X ____________

Posted on www.debteraw.com by courtesy of the author on 15 August 2007.